# ይነገረው መርዶ

ዘረፋው ግድያው ፣ ሲሆን አይን ያወጣ
ከገደቡ ሲያልፍ ፣ ጥጋብ ቅጡን ሲያጣ
ትዕግስቱን አሟጥጦ ፣ ህዝቡን ስላስቆጣ
የደደቢት ደደብ ፣ መድረክ እየወጣ
ከበሮ መጠለዝ ፣ መዝለል እንደ ፌንጣ
ከሞት አላዳነም ፣ የምጥ ቀን ሲመጣ
መቃብር ብቻ ነው ፣ የወያኔ ዕጣ ።

ፋታ በማይሰጠው ፣ በሌለው ቀጠሮ
ህዝባችን ሲፋለም ፣ በቃኝ ብሎ አምርሮ
መሸሸጊያ እንዳጣች ፣ ጭልፊት ያየች ዶሮ
እየቃዡ ማደር ፣ የመባነን ኑሮ
የምጥ ዘመን ሆኗል ፣ ለባንዳው ዘንድሮ ፣-
    አንገት ስለሌለው ፣ ስለማያይ ዞሮ
    የሚይዘው ቢያጣ ፣ ወያኔ ተሳክሮ
    ከዓይን ተሰውሮ ፣ በሹክሹክታ መክሮ
    ሲዶልት ያመሻል ፣ መቀሌ ተሻግሮ ።

ወያኔስ በልቶ ነው ፣ ይብለኝ ላራጋቢ
ከጉሮሮ እማታልፍ ፣ ለሚያገኛት ገቢ
ትዕቢት የነፋው ፣ በልቶ ቅንጥብጣቢ
የባንዳ ቅጥረኛ ፣ ሹል አፍ ተሳዳቢ
ሲያንዛርጥ የኖረ ፣ ተስፈኛ ሰላቢ
አደግድጎ አዳሪ ፣ የጠንቋይ ቀላቢ
አመዱን ነዛበት ፣ እራቀው ውቃቢ ።

እራሱን አዋርዶ ፣ ማንነቱን ሸጦ
ከህዝብ እንዳይወግን ፣ ባንዳነትን መርጦ
ቋንጣ እንዳየች ድመት ፣ አይኖቹን አፍጥጦ
አሰፍስፎ የቆመ ፣ ሊበላ ቀላውጦ
ህዝብ እንደተነሳ ፣ በአንድነት ቆርጦ
ይነገረው መርዶ ፣ ያልቅስ ተቀምጦ ፣-
    ቋንጣም እሬት ሆኗል ፣ ያኝከው አላምጦ
    ከኮሶ ቢመርም ፣ ይጠጣት በጥብጦ
    ግልግል ነው ለኛም ፣ ቢሞትም ደንግጦ
    ምንም ስላላየን ፣ ዛሬም ተለውጦ ።

ታዛቢው

April 24, 2018